ዕፅዋትን ይመልከቱ፤ ንፁህ አየር ይተንፍሱ




# በጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ውስጥ የሚሰጡ የኢኮቱሪዝም አገልግሎቶች

2016 ዓ.ም

## ራዕይ (Vision)

በ2022 ዓ.ም በምርምር፣ በሆርቲካልቸር ልማት፣ በብዝሃ ህይወት ትምህርትና በኢኮ- ቱሪዝም ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ተምሣሌታዊ የዕፅዋት ማዕከል ሆኖ ማየት።

## ተልዕኮ (Mission)

ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ከኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ሀገር በቀል፣ ብርቅዬ እና ለመጥፋት የተቃረቡ የዕፅዋት ዝርያዎች ቅድሚያ በመስጠት በማሰባሰብና በማላመድ እንዲሁም በማዕከሉ ያሉ ዝርያዎችን በመጠበቅና የምርምር ሥራዎችን በመስራት፣ በቦታዊ እና በኢ-ዘቦታዊ ዘዴዎች በማልማትና በመንከባከብ፣ ከመዋዕለ ህፃናት እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተግባር ተኮር የብዝሃ ህይወት ትምህርት ድጋፍ በማድረግ እና ተፈጥሮን መሰረት ያደረገ የመዝናኛና የኢኮቱሪዝም አገልግልት ለህብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ ነው።

## ዓላማዎች

1. በማዕከሉ፣ በአካባቢው በኢትዮጵያና በሌሎች አካባቢዎች ለመጥፋት የተቃረቡትን ዕፅዋት በማስቀደም የዝርያዎች እንክብካቤ ተግባራትን ማከናወን
2. በሥነ ሕይወት፣ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝና በሌሎች አካባቢነክ መስኮች ላይ ምርምር ማካሄድ፣
3. ከአካባቢ ጥበቃ፣ ከተፈጥሮ ሀብትና ከሥነ ምህዳር አያያዝ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ግንዛቤ የመፍጠር ዓላማ ያላቸው የአካባቢ ትምህርት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶችን ማመቻቸትና መተግበር፣
4. በተፈጥሮ ላይ የተመሰረተ የመዝናኛና የኢኮቱሪዝም አገልግሎት መስጠትና ማስፋፋት፣
5. በአካባቢ ጥበቃ መስኮች የተሰማሩ ብሄራዊና ዓለም አቀፋዊ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን መደገፍና ማበረታታት::



# ማውጫ


| ተ.ቁ | | | ገፅ |
|---|---|---|---|
| 1. | ዋና ዳይሬክተር መልዕክት | ------------ | |
| 2. | | ------------ | |
| 3. | | ------------ | |
| 4. | | ------------ | |
| 5. | | ------------ | |
| 6. | | ------------ | |
| 7. | | ------------ | |
| 8. | | ------------ | |
| 9. | | ------------ | |
| 10. | | ------------ | |
| 11. | | ------------ | |
| 12. | | ------------ | |
| 13. | | ------------ | |



# የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ዋና ዳይሬክተር መልዕክት

## የኢ/ር ጉተማ ሞረዳ ጎበና መልዕክት

ኢትዮጵያ ቁጥራቸው 6,500 የሚገመት የዕፅዋት ዝርያዎች መገኛ ስትሆን አስር በመቶ የሚሆኑ ብርቅዬ ዕፅዋት መኖሪያም ነች። ይህ ደግሞ የአለም የዕፅዋት ዝርያ መገኛ፣ የሰው ልጅ ለምግብነትና ለሌሎች የዕለት ተዕለት ፍጆታ የሚጠቀምባቸው አዝዕርት ምንጭ ወይም መነሻ ማዕከል ያደርጋታል። ለሀገራችን በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነውና የምሁራን አሻራ ያረፈበት የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ከተቋቋመ በኃላ ቀደም ሲል በውስጡ የነበሩትንና ከተለያየ የሀገሪቱ ክፍሎች የተሰበሰቡ ከ1300 በላይ ሀገር በቀል የዕፅዋት ዝርያዎችን የያዘ ሲሆን በቁጥር 65 የሚሆኑት ደግሞ የሀገራችን ብርቅዬ ዕፅዋት መሆናቸውን ቀደም ሲል የተደረገ ጥናት ያመለክታል። የማዕከሉን ዋና ዋና አላማዎች ለማሳካት እና ተጨባጭ ውጤት ለማስመዝገብ የሚከተለውን ቁልፍ መልዕክት ለማስተላለፍ እወዳለሁ።

- የዕፅዋት ማዕከሉ ሊያሳካቸው ከተቋቋመባቸው ዋና ዓላማዎች አንዱ የሆነው የምርምር ዘርፍ ነው። ምርምር የዕፅዋት ብዝሀ-ህይወት ሀብታችንን ለመጠበቅ ብሎም ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲቻል በተፈጥሮ ወይም በማህበራዊ ሳይንስና ጥናት ከመስራት ጎን ለጎን በዘርፉ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላትና ተመራማሪዎችን መሳብ፤

- የዕፅዋት ማዕከሉ በቀጣይ የሀገር በቀል ዕፅዋትን በተለይ ለመጥፋት የተቃረቡትን በማስቀደም በመንከባከብና በማልማት ብሎም የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማስፋት ለአረንጓዴ ስፍራዎች ማስዋቢያነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያስችሉ ሥራዎችን ማከናወን፤

- የዕፅዋት ማዕከሉ በሁሉም ደረጃ ለሚገኙ መምህራንና ተማሪዎች የማዕከሉን ማራኪ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የዕፅዋት ስነ-ህይወት፣ ነፍሳትንና ስነ-ምድርን ወዘተ... የተመለከቱ ተግባር ተኮር ትምህርት፣ ጥናትና ምርምሮችን ለማካሄድ የሚያስችል የመስክ ቤተ ሙከራ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል፤

- ለከተማችን ነዋሪዎች፣ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ጎብኚዎች ተመራጭ መዳረሻ የዕፅዋት ማዕከል ሆኖ ደረጃውን የጠበቀ የኢኮ ቱሪዝም አገልግሎት የሚሰጥ በተፈጥሮአዊ መስህብነቱና ከብክለት ነፃ የሆነ ንፁህ አየር መገኛ እንዲሆን ማስቻል

- ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ዋና ዋና ጉዳዮች የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ የሚያከናውናቸው ተግባራት መሆናቸውን በዚሁ አጋጣሚ እየገለፅኩ ለስኬታማነቱ የከተማው አስተዳደር፣ የማዕከሉ ማኔጅመንትና ሠራተኞች እንዲሁም ባለድረሻ አካላት ለሚያደረጉት ያልተቆጠበ ጥረት ከወዲሁ በራሴና በጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ስም ማመስገን እወዳለሁ።

**የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ዋና ዳይሬክተር እንጂነር ጉተማ ሞረዳ**

# ታሪካዊ ዳራ

በዓለማችን በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገታቸው ትልቅ ደረጃ ላይ የደረሱ ሀገራት ከተሞች የዘመናዊነታቸው መገለጫ ሰማይ ጠቀስ ህንፃዎቻቸው ብቻ አይደሉም። ወይም ደግሞ በልዩ ጥበብ በምሽት ህብረ ቀለማት ዓይንን ከግራ ወደ ቀኝ፤ ከቀኝ ወደ ግራ የሚወስዱ በሚመልሱት የቴክኖሎጂ ውጤቶች ብቻ አለመሆኑ አያከራክርም። ይልቁንም ከተጠቀሱት ዘርፎች ባልተናነሰ ትኩረት በሚቸሩት የተፈጥሮ ጥበቃ፣ የዕፅዋት እንክብካቤ ፣ የአረንጓዴ ልማትና ምርምር ሥራዎች እንጂ። ለዚህ ደግሞ ትልቅ አብነት ተደርጎ የሚወሰደው ዘርፍ የዕፅዋት ማዕከላት ሲሆን አጀማመሩ (ታሪካዊ ዳራው) እንደሚያመለክተው ከ400 ዓመታት በላይ አስቆጥሯል።

ከተቆረቆረች ከ125 ዓመት በላይ ያስቆጠረችው የአገራችንና የአፍሪካ መዲና አዲስ አበባ ተፈጥሮአዊ ይዞቱን ሣይለቅ በዘመናዊ መንገድ የሚለማ ለቀጣይ ትውልድ ትልቅ ፋይዳ ያለው የተፈጥሮ ገፀ-በረከት ባለቤት ሆናለች። ለገፀ በረከቱ እውን መሆን የአዲስ አበባ አስተዳደር ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር የከተማዋን ሰሜን ምዕራብ ዳርቻ ይዞ እስከ ኦሮሚያ ክልል አዋሰኝ ድረስ 705 ሄክታር መሬት ላይ የተንጣለለ ከከተማዋ አልፎ ተርፎ ለሀገራችን ፋና ወጊ የሆነውን ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከን አቋቁሟል።

ማዕከሉ ይዞት የተነሳውን ዓላማ ለማሳካት በአዋጅ ቁጥር 18/2002 ዓ.ም የተቋቋመ ነው። በዋነኛነት የተለያዩ የዕፅዋት ዝርያዎችን በታቀደ መንገድ በመጠበቅ እና በመንከባከብ ለሣይንሳዊ የዕፅዋት ምርምር፣ ለአካባቢያዊ ትምህርት መስጫነት እንዲሁም ተፈጥሮን መሠረት ያደረገ የመዝናኛ አገልግሎት ለመስጠት የተቋቋመ ሲሆን ዕፅዋት ማዕከሉም የተለያዩ መሠረታዊ የልማት ሥራዎችን በትጋት በመስራት ላይ ይገኛል።

ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል በሰሜን ምዕራብ አዲስ አበባ ከአዲሱ ገበያ ወደ ሱሉልታ በሚወስደው መንገድ ከአደባባዩ በስተግራ እና ከሸጎሌ ቀለበት መንገድ ወደ ዊንጌት በሚወስደው አስፋልት በስተቀኝ የሚገኝ በኢትዮጲያ በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነ የዕፅዋት ማዕከል ነው። በአብዛኛው ዳገታማ እና ከፊል ዳገታማ አካባቢዎች የሚበዙበት ሲሆን ከፍታውም ከ2713 እስከ 2950 ሜትር ከባህር ጠለል በላይ እንዲሁም አመታዊ የዝናብ መጠኑ ከ1100 እስከ 1300 ሚ.ሜ ነው።



# በዕፅዋት ማዕከሉ ውስጥ ባሉ አራት ዓላማ ፈፃሚዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች



## ➢ የቱሪዝም ልማትና ፕሮሞሽን ዳይሬክቶሬት

ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ካለው ተፈጥሯዊ አቀማመጥ ብሎም የሥነ-ምህዳር ተለያይነት እና የዱር እንስሳት ስብጥር ጋር በተያያዘ ለጎብኝዎች ዘርፈ ብዙ የኢኮ-ቱሪዝም አገልግሎቶችን በመስጠት ላይ ይገኛል። ከነዚህም ውስጥ በዋነኛነት የሚከተሉት ይገኙበታል።





## ➢ የእግር ጉዞ /hiking/

የእግር ጉዞ ጠንካራ ጡንቻዎችን እና አጥንቶችን ለመገንባት፣ የልብን ጤና ለማሻሻልና የመተንፈሻ አካላት ችግር አደጋን ለመቀነስ ከሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ አንዱ ነው። ማዕከሉ መነሻቸውን ደቡብ በር፣ ሰሜን በር፣ ሳንሱሲ፣ ችግኝ ጣቢያ እና ፓርኪንግ በማድረግ አጭር የእግር ጉዞ መስመር እስከ **4** ኪሎ ሜትር፣ መካከለኛ የእግር ጉዞ መስመር እስከ **8** ኪሎ ሜትር እና ረጅም የእግር ጉዞ መስመር እስከ **15** ኪሎ ሜትር የሚሸፍኑ የጉዞ መስመሮች አሉት።

## ➢ የከፍታእይታ/panoramic view/

የከፍታ እይታ ማለት ሙሉ በሙሉ ወይም ሰፊ እይታ ለማየት በሚያስችል ቦታ ላይ ሆኖ መመልከት ማለት ነው።

የዕፅዋት ማዕከሉን ሥነ-ምህዳር ብሎም የአዲስ አበባ ከተማን የመሬት አቀማመጥ ከፍ ባሉ ቦታ ላይ በመሆን መመልከት ለሚፈልጉ ጎብኝዎች በማዕከሉ ሶስት ዋና ዋና ከፍታ ቦታዎች ይገኛሉ። በማዕከሉ ውስጥ የሚገኘው ከፍታ ቦታ ትልቁ ደካ ቦራ በመባል የሚታወቀው ሲሆን **ደካ ቦራ** የሚለውንም ስያሜ ያገኘው ከኦሮምኛ ቋንቋ እንደሆነና ትርጉሙም ዳለቻ ድንጋይ ማለት እንደሆነ ከአፈ-ታሪክ የተገኘው መረጃ



ያስረዳናል። የዚህም ስፍራ ከፍታ ከባሕር ጠለል በላይ **2870** ሜትር ሲሆን በዕፀዋት ማዕከሉ ማዕከላዊ ስፍራ ላይ የሚገኝ ገላጣማ እና በዋነኛነት እጅግ ትልቅ ሽፋን ያለውን የተፈጥሮ ጥብቅ ደን እንዲሁም የዕፀዋት ስብጥር ለማየት ያስችላል።

የማዕከሉን ገፅታ ከበስተ ሰሜን ወደ ደቡብ አቅጣጫ ለመመልከት አመቺ ከሆኑ ቦታዎች ውስጥ ድምድም ተመራጭ የሆነ ስፍራ ነው። ድምድም የሚለው ስያሜ ሊሰጠው የቻለው ቃሉ እንደሚገልጸው ቦታው ዋሻ ያለበት በመሆኑ ሲረገጥ ድምድም የሚል ድምጽ በማሰማቱ እንደሆነ ቀደም ሲል በአፈ ታሪክ ሲነገር የቆየ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ይህ ቦታ ከባህር ጠለል በላይ እስከ **2950** ሜትር ከፍታ ሲኖረው የማዕከሉን የመሬት አቀማመጥ፣ የዕፀዋት ሁኔታ እና የአዲስ አበባ ከተማን በጉልህ ለመመልከት የሚያስችል ስፍራ ነው። በሶስተኛነት የተቀመጠው የማዕከሉ ከፍተኛ ስፍራ ትንሹ ደካ ቦራ በመባል የሚታወቅ ሲሆን ስያሜውን ያገኘው ልክ እንደ ትልቁ ደካ ቦራ ከኦሮምኛ ቋንቋ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። የዚህም ስፍራ ከፍታ ከባህር ጠለል በላይ እስከ **2713** ሜትር ነው።

## ➢ የዱር አዳር አገልግሎት /camping service/

የዱር አዳር አገልግሎት ከቤት ወይንም ከከተማ ወጣ ተብሎ ለመዝናናት ወይም ለትምህርት አዳርን ተፈጥሮን መሰረት ባደረጉ ስፍራዎች ለምሳሌ በተፈጥሮ ደን፣ ሐይቆች አካባቢ፣ የወንዝ ዳርቻዎች፣ በዕፀዋት አፀዶች፣ በማህበረሰብ አቀፍ ጥብቅ ቦታዎች እና በዱር እንስሳት ጥብቅ ስፍራዎች በጊዜያዊ መጠለያ በተለይም በድንኳን ውስጥ የማሳለፍ ተግባር ነው። በዱር አዳር ወቅት እንግዶች ምግባቸውን ማብሰል፣ የእግር ጉዞ ማድረግ፣ የተለያዩ የምርምር ስራዎችን መስራት እንዲሁም የዱር እንስሳት እና አዕዋፋትን በማየትና ድምጻቸውን በማድመጥ እየተዝናኑ ጊዜያቸውን ማሳለፍ ይችላሉ፡ ፡





## ➢ የደሴት ማረፊያ አገልግሎት /picnic service/

የደሴት ማረፊያ አገልግሎት ሰዎች በተፈጥሮ አካባቢዎች ላይ ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን በጋራና በተናጠል የሚከውኑበት ቦታ ነው፡፡

## ➢ የፊልምና የፎቶግራፍ አገልግሎት filming and photography

የፊልምና የፎቶግራፍ ፕሮግራም ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ የሚጠቀሱ ሲሆኑ ማዕከሉ ለዚህ አገልግሎት እጅግ ምቹ ነው፡፡



## ➢ የልዩ ልዩ ሁነቶች ዝግጅት /eco-friendly events/

ሁነት በየትኛውም ጊዜ ወቅትና ሰዓት፣ በየትኛውም መጠን ሊዘጋጅ ይችላል። እነስ ካሉ ሠርጎች እና ከቤተሰባዊ ዝግጅቶች ጀምሮ እስከ ሃገር መሪዎች በዓለ-ሲመት ደረስ ያሉ ክንውኖች በሙሉ ሁነት ልንላቸው እንችላለን። ከዚህ ጋርም በተያያዘ የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል የተለያየ መጠን ያላቸውን ጎብኝዎች ለማስተናገድ የሚያስችል አመቺ ስፍራዎች የያዘ በመሆኑ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የምርቃት ስነ-ስርአት እንስቶ የተለያዩ የሁነቶች ዝግጅት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው።



## ➢ ተራራ መውጣት /mountain climbing/

ተራራ መውጣት አገልግሎት፤ በተራራማ ቦታዎች ላይ ከፍ ያሉ ቦታዎችን መድረስ ወይም ለመድረስ መሞከር ማለት ነው። ተራራ መውጣት ከባድ የአካል እንቅስቃሴን፣ በእግር መራመድን፣ እለት መውጣትን እና በበረዶ የተሸፈኑ ተዳፋቶችን ማቋረጥን ያካትታል።



## ➢ ተመስጦ አገልግሎት /yoga/

ተመስጦ አካላዊና መንፈሳዊ መመሰጥን ያካተተ እንቅስቃሴ ሲሆን የአተነፋፈስ ስርዓትን፣ የሰውነት እንቅስቃሴንና መመሰጥን በውስጡ ይይዛል። ተመስጦ ጤናን ለማሻሻልና ደስተኛ ለመሆን አስተዋጽዖው የጎላ ነው።







## ➢ የሰርግ አገልግሎት / wedding

ማዕከሉ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ አንዱ የሰርግ ፎቶግራፍና ቪዲዮ ቀረጻ እንደመሆኑ ወደ ማዕከሉ ለሰርግ ዝግጅት ለሚመጡ እንግዶች ተመራጭ የሆኑ ስፍራዎች ይገኛሉ።

## ➢ የመኪና ማቆሚያ አገልግሎት / parking service

የዕፅዋት ማዕከሉ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ ለጉብኝት ለሚመጡ እንግዶች የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አንዱ ነው። በማዕከሉ ቅጥር ግቢ 150 ተሽከርካሪ የሚያስተናግድ እና ማዕከሉ መግቢያ አካባቢ 300 ተሽከርካሪ የሚያስተናግድ የመኪና ማቆሚያ የተገነባ በመሆኑ ጎብኝዎች ያለስጋት ተዝናንተው እንዲመለሱ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል።



## ➢ የካፌና ሬስቶራንት አገልግሎት /cafe and restaurant/

በማዕከሉ ውስጥ የምግብና መጠጥ አገልግሎት የሚሰጥ ስያሜው ዋርካ ሎጅ የሆነ ካፌና ሬስቶራንት ያለ ሲሆን የተለያዩ ምግቦች እና መጠጦችን ያቀርባል።






## ➢ የብስክሌት አገልግሎት/ bicycling

ብስክሌት መጋለብ በዋነኛነት የኤሮቢክ እንቅስቃሴ ሲሆን ልብ፣ ደም ስሮችና ሳንባ በአግባቡ ስራቸውን እንዲያከናውኑ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋል፡

- ከተቃጠለው ጎቶ ሳንሱሲ ተመልሰዉ በወሰርቢ መውረጃ (ቴሌ ሜዳ) መቆሚያ 6 ኪሎሜትር
- ከደቡብ በር-ሚሊኒዬም-ፍተሸ(ሰሜን በር) 4 ኪሎሜትር
- ሚሊንዬም -ቃሌ-እቡነ-ሃብተማሪያም -የተቃጠለ ጉቶ - 5 ኪ/ሜ
- ኪደነምህረት መግቢያ - ፀበል - ዳም ቢ - ሎጅ-ሚሊኒዬም - ቃሌ - እቡነ ሃብተማሪያም- የተቃጠለ ጉቶ-ሳንሱሲ 10 ኪ/ሜ

## ➢ የመኪና ማቆሚያ አገልግሎት /parking service/

የዕፅዋት ማዕከሉ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ ለጉብኝት ለሚመጡ እንግዶች የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት አንዱ ነው። በማዕከሉ ቅጥር ግቢ 150 ተሽከርካሪ የሚያስተናግድ እና ማዕከሉ መግቢያ አካባቢ 300 ተሽከርካሪ የሚያስተናግድ የመኪና ማቆሚያ የተገነባ በመሆኑ ጎብኙዎች ያለስጋት ተዝናንተው እንዲመለሱ ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል።

## ➢ የሰርግ አገልግሎት / wedding

ማዕከሉ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ አንዱ የሰርግ ፎቶግራፍና ቪዲዮ ቀረጻ እንደመሆኑ ወደ ማዕከሉ ለሰርግ ዝግጅት ለሚመጡ እንግዶች ተመራጭ የሆኑ ስፍራዎች ይገኛሉ።





# ወፎችን የመመልከት አገልግሎት

**bird watching**



**Ethiopian White-eye**



**Tacazze Sunbirds**



**Ethiopian Cisticola**

# የተለያዩ የዱር እንስሳትን የመመልከት አገልግሎት

## wildlife viewing






## Menelik's Bushbuck

**የማዕከሉ መዳረሻ ቦታዎች**

- ድምድም ተራራ አካባቢ / Dim-Dim Mountain
- ትልቁ ደካ ቦራ ተራራ አካባቢ /Tiliku Daka Bora Mountain
- ትንሹ ደካ ቦራ አካባቢ /Tinishu Daka Bora Mountain
- ጨልጨሌ አካባቢ
- ደቡብ በር የደሴት ማረፊያ አካባቢ/ South gate picnic area
- አጎራ 2 አካባቢ
- ችግኝ ጣቢያ አካባቢ
- አምፊ ቲያትር
- ፍሩት ጋርደን አካባቢ
- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አደባባይ አካባቢ
- ፏፏቴ









# የሆርቲካልቸር ዳይሬክቶሬት

**የሆርቲ ካልቸር ልማትና ዳይሬክቶሬት ዋና ዋና ተግባራት**

1. የመሬት አጠቃቀም እና የላንድ ስኬፕ ዝግጅት
2. የጋርደን ዲዛይን እና ልማት ማካሄድ
3. የመሰረተ ልማትና እድሳት ማካሄድ
4. ችግኝ ጣቢያ ልማት እና እንክብካቤ ማካሄድ
5. የዕፅዋት ስነ ውበት ልማት እና እንክብካቤ ማካሄድ
6. የአትክልትና ፍራፍሬ ሰርቶ ማሳያ፣ልማትና እንክብካቤ ማካሄድ
7. የመስኖ ልማትና እንክብካቤ ማካሄድ
8. የተፋሰስ ልማትና እንክብካቤ ማካሄድ
9. የብዝሀ ሕይወት ልማትና እንክብካቤ ማካሄድ





# የዕፅዋት ምርምር ዳይሬክቶሬት

የሀገራችንን የዕፅዋት ዝርያዎችን የመንከባከብና ቀጣይነታቸውን የሚያረጋግጥ ምርምር ማካሄድ ዋነኛ ተግባሩ ሲሆን ማዕከሉ ሲቋቋም የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው በወቅቱ የነበሩት የዕፅዋት ዝርያዎች ሁለት መቶ አርባ አይነቶች ሲሆኑ ከዚያ በኋላ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በተደረገ ዕፅዋትን የማሰባሰብ ስራ ቁጥሩን ማሳደግ ተችሏል።

በማዕከሉ ውስጥ **65** ብርቅዬ፣ **946** አገር በቀል፣ **289** መጤ የሆኑና በአጠቃላይ **1300** ዕፅዋት ይገኛሉ። በዕፅዋት ማዕከሉ እስከ **95** የሚደርሱ አዕዋፋት እና እስከ **16** የሚጠጉ አጥቢ የዱር እንስሳት ይኖራሉ ተብሎ ይታመናል።





**ለመድሐኒት የሚሆኑ የዕፅዋት አይነቶች በጥቂቱ**

1. የአይጥ ሀረግ
2. ችፍርግ
3. እሬት
4. ከሴ/ኮሰረት
5. ዳማከሴ
6. መቅመቆ
7. ቀጨም
8. ጥቁር እንጨት
9. ጤናዳም
10. እንስላል
11. የእህያ ጆሮ

**ለውበት የሚሆኑ የዕፅዋት አይነቶች በጥቂቱ**

1. አምጃ
2. ግራዋ
3. ኔፎሪያ
4. ኮሠረት/ዳማከሴ
5. ቀጋ
6. Pelargonium
7. Geranium
8. Shemsire
9. Silver







❖ ብዝሃ-ህይወት ትምህርት ዳይሬክቶሬት

## የብዝሃ-ህይወት ትምህርት ዋና ዋና አገልግሎቶች

1. በተግባር ተኮር የአካባቢና ስነ-ምህዳር ትምህርት እና ግንዛቤ አገልግሎት መስጠት
2. ስልጠና አገልግሎት መስጠት
3. የግንዛቤ አገልግሎት መስጠት

## የተግባር ተኮር ትምህርት





## የግንዛቤ አገልግሎት መስጠት





## የስልጠና አገልግሎት መስጠት





# መሰረተ ልማት

ማዕከሉን ለተገልጋዩ የህብረተሰብ ክፍል በተሻለ ሁኔታ ተደራሽ እና ምቹ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ የመሰረተ ልማት ስራዎች በመከናወን ላይ ናቸው።





የውስጥ ለውስጥ የኮብልስቶን መንገድ መፀዳጃ ቤቶች ዋርካ ሎጅ

መመልከቻ ማማ ሰፊና ምቹ የመኪና ማቆሚያ ትንሿ አዳራሽ









የህፃናት መጫዎቻ ለፎቶና ለሰርግ የሚሆኑ ቦታዎች





ጎጆ ቤቶች አጎራ 2 አንፊ ቲያትር



አጎራ 1

## የጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል አገልግሎት ለማግኘት

በአካል ትኬት ለመቁረጥ በማዕከሉ መግቢያ በር ላይ

**በሲቢኢ** ብር 100003784488

**ቴሌ ብር** የድርጅቱ አጭር ቁጥር /short code 788138

ኦፕሬተር መለያ ቁጥር /operator ID 227375/382978 መክፈል ይችላሉ።

## ለበለጠ መረጃ

- 011 1 54 79 39 (የቢሮ)
- 011 1 54 70 61 (የቢሮ)
- 011 1 54 68 05 (የቢሮ)
- 09 37 80 67 11 (ሞባይል)

fecebook : ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል-Gullele Botanical Garden

Telegram : Gullele Botanic Garden communication and Ict dep

## የስራ ሰዓት

- የቢሮ ከሰኞ-አርብ 2፡30-11፡30
- የመስክ እሁድ 2፡30-11፡30








**ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል**
Gullele Botanic Garden

011 1 54 79 39 (የቢሮ)
011 1 54 70 61 (የቢሮ)
011 1 54 68 05 (የቢሮ)
09 37 80 67 11 (ሞባይል)
fecebook : ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል-Gullele Botanical Garden
Telegram : Gullele Botanic Garden communication and Ict dep